**Español:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_spanish.pdf
**Kreyòl ayisyen:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_hcreole.pdf
**বাংলা:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_bangla.pdf
**አማርኛ:** masspowerchoice.com/cambridge/letter_amharic.pdf
masspowerchoice.com/cambridge/letter_arabic.pdf **عربى**

# የካምብሪጅ ከተማ

## የማሕበረሰብ የመብራት/ኤሌክትሪክ ቅንብር ፕሮግራም (COMMUNITY ELECTRICITY AGGREGATION PROGRAM)

**የማስታወቅያ ደብዳቤ**

ህዳር (November) 19 ቀን 2024

የተከበራችሁ የካምብሪጅ ነዋሪዎች ወይም የንግድ ስራ ባለቤቶች፡

ይህ ደብዳቤ የኤሌክትሪክ ክፍያዎን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃ የያዘ ነው።

በአሁኑ ወቅት ፡ ኤቨርሶርስ ቤዚክ አገልግሎት (Eversource Basic Service) በሚባል የመብራት/የኤሌክትሪክ አገልግሎት ነው በመገልገል ላይ የሚገኙት። ይህም ማለት የመብራት/ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያገኙት ኤቨርሶርስ (Eversource) ከሚባለው የኤሌክትሪክ ተቋም ነው። ይሄው ተቋም መብራት እንዲደርሶት ያደርጋል። እሱም ነው መብራት ወይም ኤሌትሪክ ከሌሎች የሚገዛሎት ማለት ነው።

ይሁንና የካምብሪጅ ከተማ፤ የካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ (Cambridge Community Electricity-ሲ-ሲ-ኢ-CCE) የሚባል ፕሮግራም አለው። በዚህ ፕሮግራም ኤቨርሶርስ (Eversource) ኤሌክትሪክ ያቀርብሎታል፣ ከተማው ግን የራሱን የኤሌክትሪክ አቅራቢ ይመርጣል። ከተማው ይህንን ፕሮግራም ከጸሃይ የሚመነጭ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል በካምብሪጅ ለመፍጠር ይጠቀምበታል። የእርሶ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ፤ አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲጨመር ያግዛሉ ማለት ነው።

**ይህንን ደብዳቤ ካገኙ በኋላ ምንም መልስ ካልሰጡ፤ በኦቶማቲክ መንገድ በካምብሪጅ የማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) ውስጥ ይገባሉ።**

**በፕሮግራሙ ውስጥ ኦቶማቲክ ምዝገባን ለማስወገድ፤ ከፕሮግራሙ መውጣት መፈለጎን የሚገልጸው ደብዳቤዎ ፖስታ ቤት የገባው ከ ታህሳስ (December) 23 ቀን 2024 በፊት መሆኑን ከሚያሳይ ምልክት ጋር መላክ አለበት።**

**የሚሳተፉባቸው መንገዶች:** ኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ መሆኑን ይቀጥላል። የኤሌክትሪክ ክፍያዎን መክፈል የሚቀጥሉት ኤቨርሶርስ (Eversource) ነው፤ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ቢቋረጥቦት የሚደውሉትም እነሱ ጋ ነው። ከኤቨርሶርስ (Eversource) በሚደርሶት የክፍያ ወረቀት ላይ ግን ኤሌክትሪክ የሚያቀብሎት ዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy) የሚል ተመዝግቦ ያያሉ፤ በካምብሪጅ የማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) የክፍያ ዋጋ መጠን መሰረትም ክፍያዎ ምን ያህል እንደሆነ በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) እንደሚተመን በክፍያ ወረቀትዎ ላይ ተጽፎ ያገኙታል።

**አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች የሚደረግ የአቅርቦት መጠንና የነዳጅ እገዛ ለማግኘት ብቁ ሆነው ተገኝተው ከነበሩ፡ እነኝያኑ ጠቀሜታዎችን ማግኘትዎን ይቀጥላሉ። በዛው ሲደረግሎት በቆየው የእገዛ መጠን ይቀጥላሉ።**

**ላለመሳተፍ ማምረጥ:** ኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ መሆኑን ይቀጥላል። በክፍያ ሂሳቦ ላይ ያለው የአቅራቢ ክፍያ በኤቨርሶርስ (Eversource) መሰረታዊ የዋጋ አገልግሎት (Eversource's Basic Service) መሰረት መታሰቡን ይቀጥላል።

### የመሳተፍ ጠቀሜታ

**የአካባቢ የሚታደስ ኤሌክትሪክ (renewable electricity)** - ከተማው፤ አዲስ የሚታደስ የኤሌክትሪክ አገልግሎት በሰንጠረዡ ውስጥ ለመደመር፣ በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) አማካኝነት የተሰበሰበውን ገንዘብ ይጠቀማል። ከከተማው አዲስ የ ጸሃይ ኤነርጂ ፕሮጀክት የሚገኘው ይህ የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል፤ አረንጓዴ ኤሌክትሪክ (green electricity) በማምረት፤ የሲሲኢ (CCE) ደንበኞችን የኤሌክትሪክ አቅርቦትን የሚነካ የግሪንሀውስ የጋዝ ግኝትን (greenhouse gas) ዝቅ እንዲል ያደርጋል።

**አማራጮች** - ፕሮግራሙ ሶስት አማራጮችን ይሰጦታል፤ 1) 100% ግሪን ፐላስ (Green Plus)፤ ይህም 100% ከኤም ኤ ክፍል 1 (MA Class I) የሚገኝ የሚታደስ ኤነርጂን ያጠቃልላል። 2) ስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) ደግሞ 50% ከኤም ኤ ክፍል 1 (MA Class I) የሚገኝ የሚታደስ ኤነርጂ ፕሮጀክት ሲያጠቃልል 3) ኤኮኖሚ ግሪን (Economy Green) የክፍለ ሃገር ህግ የሚጠየቀውን በአነስተኛ ዋጋ የሚገኘውን የሚታደስ ኤነርጂን ያካትታል። **እርሶ በኦቶማቲክ መንገድ በ ስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) ውስጥ ይመዘገባሉ። (የዚህ ዝርዝር ከበሰኋላ ይገኛል)**

**ሊሆን የሚችል የገንዘብ ቁጠባ** - በፕሮግራሙ የሚከፈለው ዋጋ ኤቨርሶርስ (Eversource) ከሚያስከፍለው መደበኛ የአገልግሎት ዋጋ ዝቅ ሊል ይችላል። ይሁንና የኤቨርሶርስ (Eversource) መደበኛ ዋጋ በተለያዩ ወቅቶች (seasonally) ይለዋወጣል። **በዚህም ምክንያት የፕሮግራሙ ዋጋ ሁሌም ከኤቨርሶርስ (Eversource) ዋጋ ዝቅ ይላል ለማለት አይቻልም ይሆናል፤ የገንዘብ ቁጠባም ይኖራል ተብሎ ዋስትና መስጠት አይቻልም።**

---

## የካምብሪጅ ማህበረሰብ የ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

(Cambridge Community Electricity Program)

**አዲሱ የመብራት አገልግሎት ክፍያ**

**14.81 ¢/kWh**

**ከኤቨርሶርስ (Eversource) የመኖርያ ቤቶች የአገልግሎት መደበኛ አከፋፈል ጋር ያነጻጽሩ፡**

**15.772 ¢/kWh**

የኤቨርሶርስ (Eversource) የአገልግሎት ዋጋዎች ከበስተጀርባ ይገኛሉ። ▶

---

## የደንበኛ እገዛ:

**1-844-379-9934**

## መሳተፍ አይፈልጉም?

**መሳተፍ ካልፈለጉ፡ ግዴታ የለቦትም ፤ ከፕሮግራሙ ለመውጣት የሚከፍሉት መቀጮ ወይም ገንዘብ የለም፡ ባፈለጉበት ግዜ ከፕሮግራሙ ሊወጡ ይችላሉ።**

ላለመሳተፍ ከመረጡ፡ በኤቨርሶርስ (Eversource) መሰረታዊ አገልግሎት ደንበኛ ሆነው ይቀጥላሉ።

በፕሮግራሙ ውስጥ ከመመዝገብዎ በፊት ለመውጣት ከ **ታህሳስ (December) 23 ቀን 2024** በፊት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ያድርጉ፡

- ▶ አብሮ የመጣሎትን ካርድ ይፈርሙና ይላኩት።
- ▶ አንላይን ወደ **MassPowerChoice.com/Cambridge** በመግባት ሊወጡ ይችላሉ።
- ▶ ወደ ደንበኞች አገልግሎት ክፍል በስልክ ቁጥር **1-844-379-9934** ይደውሉ።

## የካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) አማራጮቻችን፤

ከወደታች ያለው ሰንጠረዥ፤ አሁን ባሉበት ፕሮግራም መቆየት፣ ወደ ሌላ አማራጭ ፕሮግራም መሻገር ወይም ከፕሮግራሙ ወጥተው ወደ ኤቨርሶርስ መደበኛ አገልግሎት መመለስ ከሚሉት አማራጮች ውስጥ አንዱን ለመምረጥ እንድትችሉ ያግዝዎታል። ለውጥ ለማድረግ ወደ MassPowerChoice.com/Cambridge ገብተው ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-844-379-9934 ወደ ደንበኞች አገልግሎት ክፍል በመደወል፤ ከከተማይቱ የፕሮግራም አማካሪዎች ጋር ተመካከሩ።

**የካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program options) አማራጮች:**

እዚህ ላይ፤ ለመግባት ይመዘገባሉ ▼

**ለመካፈል ካልፈለጉ፤**

| | **100% ግሪን ፕላስ (100% Green Plus)** ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) 100% የሚታደስ የሃይል ፕሮጀክት | | | **ስታንዳርድ ፍሪን (Standard Green)** ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) 50% የሚታደስ የሃይል ፕሮጀክት | | | **ኤኮኖሚ ግሪን (Economy Green)** በህግ የሚፈቀድ አነስተኛው የሚታደስ ኤነርጂ/ ሃይል | | | **የኤቨርሶርስ (Eversource) መደበኛ አገልግሎት** ከፕሮግራሙ ከወጡ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ዋጋ** | **16.82 ¢/kWh*** | | | **14.81 ¢/kWh*** | | | **13.82 ¢/kWh*** | | | **15.772 ¢/kWh** - መኖርያ ቤቶች<br>**15.677 ¢/kWh** - ትናንሽ ንግድ ቤቶች<br>**17.709 ¢/kWh** - ትላልቅ ንግድ ቤቶች | | |
| **የዋጋ ወቅት (Price period)** | ምዝገባ - ጥር (January) 2026 | | | ምዝገባ - ጥር (January) 2026 | | | ምዝገባ - ጥር (January) 2026 | | | ነሓሴ (August) 1 ቀን 2024 እስከ ጥር (January) 31 ቀን 2025 የመኖርያ ቤቶችና አነስተኛ የንግድ ቤቶች፤ ከህዳር (November) 1 ቀን 2024 እስከ ጥር (January) 31 ቀን 2025 ትላልቅ የንግድ ቤቶች። | | |
| | **2024** | **2025** | **2026** | **2024** | **2025** | **2026** | **2024** | **2025** | **2026** | **2024** | **2025** | **2026** |
| **ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) የሚገኝ የሚታደስ የኤነርጂ ፕሮጀክቶች**** | | | | | | | | | | | | |
| በካምብሪጅ የተጨመረ | 76% | 73% | 70% | 26% | 23% | 20% | - | - | - | - | - | - |
| በክፍለሃገሩ ህግ የሚጠየቅ | 24% | 27% | 30% | 24% | 27% | 30% | 24% | 27% | 30% | 24% | 27% | 30% |
| **ድምር** | **100%** | **100%** | **100%** | **50%** | **50%** | **50%** | **24%** | **27%** | **30%** | **24%** | **27%** | **30%** |
| **ከሌሎች ንጹህ ወይም የሚታደስ ምንጮች የሚገኝ ኤሌክትሪክ **** | | | | | | | | | | | | |
| በክፍለሃገሩ ህግ የሚጠየቅ | 38% | 36% | 39% | 38% | 36% | 39% | 38% | 36% | 39% | 38% | 36% | 39% |
| **የአወጣጥ አገባብ** | ባፈልጉት ግዜ ይውጡ የሚከፈል የመውጫ ክፍያ የለም። | | | ባፈልጉት ግዜ ይውጡ የሚከፈል የመውጫ ክፍያ የለም። | | | ባፈልጉት ግዜ ይውጡ የሚከፈል የመውጫ ክፍያ የለም። | | | ባፈልጉት ግዜ ይውጡ። የሚከፈል የመውጫ ክፍያ የለም። ይሁንና ትላልቅ ንግድ ቤቶች ሂሳባቸውን የሚያስተካክል ወይም ብድር እንዳለባቸው የሚያሳይ ወረቀት ሊደርሳቸው ይችላል። | | |

* ዋጋዎች፤ ለአስተዳደር ክፍያ ለአንድ ኪሎዋት $0.00075/kWh ክፍያ ይጨምራሉ። ዋጋዎች በተጨማሪ፤ ለካምብሪጅ የሚታደስ ኤነርጂ ድጋፍ ለመስጠት፤ የስራ ማካሄጃ ለአንድ ኪሎዋት $0.002/kWh ክፍያ ያክላሉ። በዚህ በኤሌክትሪክ አቅርቦት ስምምነት ግዜ ውስጥ፤ የህግ ለውጥ ሲደረግ በሚያስከትለው የቁሳቁሶች ቀጥታዊ የዋጋ ጭማሪ ምክን ያት የፕሮጋራሙ ዋጋም በዛው መጠን ከፍ ሊል ይችላል።

** የማሳሹሴት ኮመንዌልት (Commonwealth of Massachusetts)፤ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ቁሳቁሶች ሁሉ በ2024- 62%፣ በ2025 ደግሞ 63% እና በ2026 የ 69% ሃይላቸውን ከንጹህ ወይም ከሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫዎች መግዛት አለባቸው ይላል። ዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy) ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) የሚታደስ ኤኔርጂ ፕሮጀክቶችና ከሌሎች የቆሻሻ፣ የኤነርጂ ወይም የኑክሊየር ምንጮች የኤሌክትሪክ ሃይል መግዛት አለበት። የኤኮኖሚ ግሪን (Economy Green) አማራጭ፤ ከሚጠየቀው ውስጥ አነስተኛውን ያሟላል። የስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) እና የ100% ግሪን ፕላስ (100% Green Plus) አማራጮች ከሱ የሚበልጡት ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) የሚታደስ የኤነርጂ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ ኤሌክትሪክ ስለሚገዙ ነው።

## ተጨማሪ መረጃ

**ይህንን ደብዳቤ ካገኙና ከሌላ ኤሌክትሪክ ከሚያቀርብ ድርጅት ጋር ውል የተፈራረሙ ከሆኑ፤ ውሉን የፈረሙት ይህ ደብዳቤ ከመላኩ በፊት ሊሆን ይችላል።** ምርጫዎ ከሆነው ከኤሌክትሪክ አገልግሎት አቅራቢ፤ ኤሌክትሪክ ማግኘትዎን ለመቀጠልና ከግዜዎ በፊት ስለወጡ የሚከፈለውን መቀጮ ከመክፈል ለመዳን፤ ከካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) መውጣት አለቦት።

**ከግብር ነጻ የሆነ ሂሳብ ካሎት፤** ከግብር መክፈል ነጻ መሆንዎን የሚያሳይ ዶኩመንት ለዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy) የማቅረብና ከግብር መክፈል ነጻ እንድትሆኑ የመጠየቅ ሃላፊነት የራስዎ ነው። ይህንን በተመለከተ በበለጠ ለመረዳት MassPowerChoice.com/Cambridgeን ይጎብኙ።

**በጣራዎ ላይ ከጸሃይ የሚገኝ ኢኔርጂ ለማግኘት የሚያስችል መሳርያ ካሎት ወይም በማህበረሰቡ የጸሃይ ኤነርጂ ፕሮግራም የሚሳተፉ ከሆነ፤** የጸሃይ ኤነርጂ ብድሮች እና ወይም የጸሃይ ኤነርጂ ማበረታቻ ክፍያዎችን ማግኘትዎን ይቀጥላሉ። በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) መሳተፎ የሂሳቡ መሰላት ላይ ለውጥ አያመጣም።

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካልዎት፣ እባክዎን ከደንበኞች እገዛ ክፍል አባሎች (customer support) ጋር በ **1-844-379-9934** ደውለው ይገናኙ ወይም ወደ **cambridge@MassPowerChoice.com** ይጻፉ፣ ወይም በኢንተርኔት ወደ **www.MassPowerChoice.com/Cambridge** ይግቡ። የፕሮግራማችን አማካሪዎች እርስዎን ለመርዳት ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ ወይም ደግሞ የካምብሪጅ ከተማን በቀጥታ በ 1-617-349-5323 ማግኘት ይችላሉ።

ይ-አን ሁዋንግ (Yi-An Huang)
የከተማ አስተዳዳሪ (City Manager)

# የካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

X ____________________________________________

ፊርማ ቀን

## የመውጫ መመርያዎች

በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ ከፈለጉ ምንም አይነት እርምጃዎችን መውሰድ አይኖርቦትም።

**በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ካልፈለጉ፤ መውጣት አለቦት።** የሚወጡት መንገድ ፖስታ በመላክ ከሆነ፡

1. **በዚህ ካርድ ላይ ቀኑን ጽፈው ይፈርሙ**
2. **ካርዱን በተካተተው ፖስታ ውስጥ ያሽጉ**
3. **ፖስታውን በፖስታ ቤት በኩል ይላኩ**

ይህ ካርድ፤ ስሙ በካርድ ላይ በተጻፈው የመዝገብ ቤት ሹም መፈረም አለበት። ከአቶማቲክ ምዝገባ ለመዳን ደግሞ የሚላክበት ፖስታ፤ ፖስታ ቤት የገባው ከ ታህሳስ (December) 23 ቀን 2024 በፊት እንደሆነ የሚያሳይ ምልክት ያለበት መሆን አለበት። በማንኛውም ግዜ ከፕሮግራሙ ለመውጣትም ወደ MassPowerChoice.com/Cambridge ይግቡ ወይም ወደ ደንበኞች አገልግሎት ክፍል በ ስልክ ቁጥር 1-844-379-9934 ይደውሉ።